# አርቲክል

በህያው ተስፋዬ

## የባህር በር

### የባህር በር የማግኘት ተፈጥሯዊ እና ዓለም አቀፋዊ መብት ነው፡፡

የሰው ልጆችን ሁሉ የመኖር፣ የመስራት፣ ሀብት የማፍራትም ሆነ ሌሎች መብቶች ተጠቃሚ ከሚያደርጉ ስርአቶች ዋናው የህግና ደንብ ተፈፃሚ መሆን ነው፡፡

በግለሰብና ግለሰብ መካከል፣ ተቋም ከተቋም፣ ሀገራትም እርስ በርሳቸው መብታቸውን የሚያስከብርበትና ግዴታቸውን የሚወጡበት በርካታ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ህጎች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የዓለም አቀፍ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት የባህር በርን የመጠቀም መብትን የሚደነግገው ህግ አንዱ ነው፡፡

በምንም አጋጣሚ ቢሆን ለወደብ መቅረብና የወደብ ባለቤት መሆን ለኢኮኖሚያዊ ዕድገትም ሆነ ለአገር ዕድገት እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ለመሆኑ ግልጽ፡፡ ይህን አባባል ቅቡል የሚያደርገው እውነታ ደግሞ ከኤርትራና ከሶማሊያ ሀገራት ውጭ የወደብ ባለቤት የሆኑ ሌሎች የዓለም ሀገራት በሙሉ ባለከፍተኛ ኢኮኖሚ መሆናቸው ነው፡፡ እነ አሜሪካ፣ ሩሲያ፣ ቻይና፣ ጃፓንና ብዙዎቹ የአውሮፓና ላቲን አሜሪካ አገሮች ለኢኮኖሚ ጥንካሬያቸው ብቻ ሳይሆን ለደኅንነታቸውም ቢሆን ወሳኝ ሀብታቸው የባህር በራቸው ወይም ወደባቸው ነው፡፡

በዓለም ላይ 44 ወደብ አልባ አገሮች ሲኖሩ ከእነዚህ ውስጥ 31 ያህሉ (70 በመቶ) ደሃዎች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያም ከእነዚህ አገሮች ተርታ ትመድባለች፡፡ እነዚህ ወደብ አልባ ደሃ አገሮች ወደ ውጭ የሚልኳቸው ምርቶቻቸው በአንድና በሁለት ሰብሎች ወይም በአንድና በሁለት የኢንዱስትሪ ውጤቶች ወይም ጥሬ ዕቃ የተወሰኑ ናቸው ፡፡

ምክንያቱም ወደብ የሌላቸው ሀገሮች ከሌላው ዓለም ጋር በሚያደርጉት የንግድ እንቅስቃሴ በተለይ የወደብ ኪራይ ተመጣጣኝ ያለመሆንና በየጊዜው ያልተገባ ጭማሪ የሚጠይቅ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የሸቀጦቻቸው ምልልስ ውድና ጊዜ የሚፈጅ መሆናቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የባህር መዳረሻ ማጣት ለአንድ ሀገር በፖለቲካ፣ በወታደራዊ እና በኢኮኖሚ ትልቅ ኪሳራ ለመሆኑም ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የባሕር ሕግ አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት በአካባቢያቸው ካለው ባሕር የተፈጥሮ ሀብት እኩል የመጠቀም መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ይህም፣ ዓሳ ማጥመድን እና በባሕር ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ፍለጋን ጨምሮ ሌሎች ከባሕር ተፈጥሮ ሀብት ጋር የተያያዙ ሀብቶች ተጠቃሚነት መብትን ያካትታል፡፡ 169 የዓለም ሀገሮች የፈረሙበትና እ.ኤ.አ. በ1982 የወጣው ዓለም አቀፍ የባህር ሕግ (United Nations Convention on the Law of the Sea/UNCLOS)፣ የዓለም ሀገሮች የባህር ክልልና ወሰንን በምን መንገድ መጠቀም እንደሚገባቸው መሠረታዊ መርሆዎችን አስቀምጧል፡፡ እ.ኤ.አ. በ1994 ወደ ሥራ የገባው ሕጉ የጠረፍንና የዓለም አቀፍ ውኃ ክልልን ምንነትና አጠቃቀም፣ እንዲሁም በባህር ወሰኖች የሚነሱ ውዝግቦችና የችግር አፈታት ሒደቶችን በዝርዝር አስፍሯል፡፡

ለዚህም ምክንያት ነው የባህር በር የማግኘት ተፈጥሯዊ እና ዓለም አቀፋዊ መብት ነው የሚባለው፡፡



እ.ኤ.አ. በ1963 በተቋቋመው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (OAU) ወይም በአፍሪካ ህብረት (AU) ቻርተርም መግቢያው ላይ በግልፅ እንደሰፈረው የአፍሪካ ሀገራት የባህር በር የሌላቸውን ጨምሮ የባህር ላይ ተጠቃሚ የመሆን መብት እንዲኖራቸው በተለይ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በባህር ላይ የመጠቀም መብታቸው እንዲጠበቅ እውቅና ይሰጣል፡፡

ለምሳሌ አፍሪካ ውስጥም  ኮንጎ ኪንሻሳና ኮንጎ ብራዛቪልን ማንሳት ይቻላል፡፡ ኮንጎ ብራዛቪል ወደብ አልነበራትም፡፡ ሁለቱም ተስማምተው ከኮንጎ ኪንሻሳ የተወሰነ መሬት ወስደው ኮንጎ ብራዛቪል ወደ ባህር እንድትዘልቅ ተደርጓል፡፡

ስለዚህ የባህር በር ያላቸው ሀገሮች መብትና ዓለም አቀፍ ግዴታን በግልጽ የሚያስቀምጠው ይህ ሕግ በተለይ ከአንቀጽ 24 እስከ 26 ባለው ክፍል የባህር በር ባለቤት ነኝ በሚል ብቻ ሀገሮች እንዳሻቸው የመሆንና የማድረግ መብት እንደሌላቸው በቀጥታ ያብራራል፡፡ የባህር ወሰናቸውን ለሰላማዊ እንቅስቃሴ እስከሆነ ድረስ ለሌሎች ሀገሮች ዝግ ማድረግ በፍጹም እንደሚከለከሉ ያትታል፡፡

በተጨማሪም የባህር በር ያለው ሀገር የባህር በር የሌለውን ሀገር የባህር ንግድ እንቅስቃሴ ማወክ እንደማይችል ማረጋገጫ የሚሰጥ ነው፡፡ የወደብና ትራንዚት አገልግሎት ላይ ሆን ብሎ መጓተት መፍጠር፣ ያልተመጣጠነ ክፍያ መጠየቅ እንደዚሁም ሆነ ከስምምነት ውጪ የሆኑ ነገሮችን ካላስፈጸምኩ ማለት የተከለከለ መሆኑንም ያመለክታል፡፡ ሕጉ የባህር በር ያላቸው ሀገሮች የባህር በር የሌላቸው ሀገሮችን ህልውናና ብሔራዊ ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥል እንቅስቃሴ ከማድረግ መቆጠብ እንዳለባቸውም ያስውቃል፡፡

በመሆኑም በአገራችንም በየጊዜው እያደገ የመጣውን የህዝብ ቁጥር ተከትሎ ባለፉት አስር አመታት ውስጥ በአማካይ የወጪና ገቢ ንግዱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ይህ የሚያመላክተው ደግሞ በሚቀጥሉት አመታት ቁጥሩ በእጥፍ ሊያድግ እንደሚችል ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለወጪ ንግዱ መፍትሔ ሊሰጡ የሚችሉ የወደብ አማራጮችን ለማግኘት ከጎረቤት ሀገራት ከፍተኛ ንግግርና ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች የተካሔዱ ቢሆንም ለወደብ ኪራይ የሚጠይቀው ወጪ ግን አሁንም የሚቀመስ የሆነ አይደለም፡፡

ስለሆነም ለኢትዮጵያ ከጅቡቲ በተጨማሪ አስተማማኝ የወደብ አማራጭ ማግኘትን የግድ ያደርገዋል፡፡